መልእክት አምስት

## እውነታ በኢየሱስ እንዳለ ክርስቶስን በመማር
## በባሕላችን ፈንታ የአንዱ አዲሱን ሰው ሕይወት መኖር

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፡- ኤፌ. 4፡20-21፣ ማቴ. 11፡18-30፣ 14፡19፤ ዮሐ. 5፡19፣ 30፤ 7፡18፤ 10፡30

**I. የኑሮ መለኪያችን በባሕላችን መሠረት ሳይሆን በኢየሱስ ባለው እውነታ፣ በምድር ላይ ሳለ በጌታ ኢየሱስ በተኖረው እውነታ መሠረት መሆን አለበት—ኤፌ. 4፡20-21፡-**

ሀ. ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ የኖረበት መንገድ አንዱ አዲሱ ሰው ዛሬ ሊኖርበት የሚገባው መንገድ ነው—ማቴ. 11፡28-30፤ ዮሐ. 6፡57፤ 4፡34፣ 5፡17፣ 19፡30፤ 6፡38፤ 17፡4።

ለ. *እውነትም በኢየሱስ እንዳለ* (ኤፌ. 4፡21) የሚያመለክተው በአራቱ ወንጌላት ውስጥ የተዘገበውን የኢየሱስን ሕይወት እርግጥ እውነታ ነው፤ ኢየሱስ ሁሉንም ነገር በእግዚአብሔር ውስጥ፣ ከእግዚአብሔር ጋርና ለእግዚአብሔር ያደረገበትን ሕይወት ኖረ፤ እግዚአብሔር በኑሮው ውስጥ ነበር ከእግዚአብሔርም ጋር አንድ ነበረ።

ሐ. ኢየሱስ ሁልጊዜ ከእግዚአብሔር ጽድቅና ቅድስና ጋር በሚስማማ መንገድ ኖረ፤ በኢየሱስ ሕይወት የእውነታው ጽድቅና ቅድስና ሁልጊዜም ሲታዩ ነበር—ቁ. 24፡-

1. የኢየሱስ የሰብዕና ኑሮ በእውነታው መሠረት፣ ማለትም ጽድቅና ቅድስና በተሞላው በእግዚአብሔር በራሱ መሠረት ነበር።
2. አዲሱ ሰው የተፈጠረው በዚህ እውነታ ጽድቅና ቅድስና ውስጥ ነው—እግዚአብሔር ሲከብር እና ሲገለጥ።

መ. የእውነታ ሕይወትን ለመኖር ክርስቶስን መማርና በእርሱ የተማርን መሆን ያስፈልገናል፤ ክርስቶስን መማር ወደ ክርስቶስ ምሳሌ (ሞዴል) ቅርጽ ውስጥ መሠራት ማለትም የክርስቶስን መልክ መምሰል ነው—ቁ. 20-21፤ ሮሜ 8፡28-29፤ 2 ዮሐ. 1፤ ዮሐ. 4፡23-24።

ሠ. ብዙዎች እንደተካተቱበት ማንነት፣ እውነታ በኢየሱስ እንዳለ፣ አዲሱ ሰው የእውነታን ሕይወት—እግዚአብሔርን የሚገልጥ ሕይወት መኖር አለበት።

ረ. በአእምሮአችን መንፈስ መሠረት ከኖርን፣ ብዙዎች የተካተቱበት አዲስ ሰው የየዕለት ኑሮ—በኢየሱስ ውስጥ ካለው እውነታ ጋር የሚስማማ ኑሮ ይኖረናል—ኤፌ. 4፡23።

**II. የአንዱ አዲሱ ሰው ኑሮ ከኢየሱስ ኑሮ ጋር ፍጹም አንድ አይነት መሆን አለበት፤ ብዙዎች የተካተቱበት አምላክ-ሰው ለሆነው ለአንዱ አዲሱ ሰው፣ የአምላክ-ሰው ኑሮ መኖር ያስፈልገናል—ፊልጵ. 1፡19-21፤ 3፡10፤ ኤፌ. 4፡20-21፡-**

ሀ. የክርስቶስ የሰብዕና ኑሮ የእግዚአብሔርን ባህሪያት በሰብዕና ሰናይ ባህሪያት ውስጥ ለመግለጥ ሰው እግዚአብሔርን ሲኖረው ነበር፤ የሰብዕና ሰናይ ባህሪያቱ በመለኮታዊ ባህሪያት ተሞልተው፣ ተዋሕደው እና ተጥለቅልቀው ነበር (ሉቃ. 1፡26-35፤ 7፡11-17፤ 10፡25-37፤ 19፡1-10)፡-

1. ጌታ ኢየሱስ በምድር ላይ ሳለ፣ ሰው ቢሆንም እንኳን የኖረው በእግዚአብሔር ነበር—ዮሐ. 6፡57፤ 5፡19፣ 30፤ 6፡38፤ 8፡28፤ 7፡16-17።
2. ጌታ ኢየሱስ በሁሉ ነገር እግዚአብሔርን ኖረው ገለጠውም፤ የትኛውንም ያደረገው ነገር ከእርሱ ውስጥና በእርሱ በኩል የእግዚአብሔር ድርጊት ነበር—14፡10።
3. ጌታ ኢየሱስ የኖረው ኑሮ ፍጹም በሆነ መልኩ በእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ መሠረትና ለእግዚአብሔር አዲስ ኪዳን ኢኮኖሚ እንደሆነ የማርቆስ ወንጌል ይገልጣል።

ለ. እንደ የመጀመሪያው አምላክ-ሰው መስፋት፣ መጨመር፣ መባዛትና መቀጠል፣ እርሱ የኖረውን አይነት ኑሮ መኖር አለብን—1 ዮሐ. 2፡6፡-

1. የጌታ የአምላክ-ሰው ኑሮ ለእኛ የአምላክ-ሰው ኑሮ ሞዴልን አስቀምጧል—እግዚአብሔር በሰብዕና ይገለጥ ዘንድ ለመኖር መሰቀል—ገላ. 2፡20።
2. ራሳችንን ልንክድ፣ የክርስቶስን ሞት ልንመስልና በመንፈሱ የተትረፈረፈ አቅርቦት ክርስቶስን ልናጎላ ያስፈልጋል—ማቴ. 16፡24፤ ፊልጵ. 3፡10፤ 1፡19-21።
3. እኔነትን ማጎልበት መቃወም እና የፍጥረታዊው ሰው መገንባትን መኮነን አለብን፤ የክርስትና ሰናይ ባህሪያት መሠረታዊ በሆነ መልኩ ከመለኮታዊው ሕይወት፣ ከመለኮታዊው ባህሪይና ከራሱ ከእግዚአብሔር ጋር የተዛመደ እንደሆነ መገንዘብ አለብን—ገላ. 5፡22-23።

4. የአምላክ-ሰውን ሕይወት የኖረው እርሱ አሁን በእኛ ውስጥና በእኛ በኩል የሚኖረው መንፈስ ነው፤ ከእርሱ በቀር የትኛውም ነገር እንዲሞላን እና እንዲይዘን መፍቀድ የለብንም—2 ቆሮ. 3፡17፤ 13፡5፤ ኤፌ. 3፡16-19።
5. በሉቃስ 6፡36 ያለውን ትዕዛዙን ለመቀበል (በጸሎት መንፈስ እና ከባቢ ሁኔታ) መላው ማንነታችንን ለጌታ መክፈት ያስፈልገናል፦ "አባታችሁ ርኅሩኅ እንደ ሆነ ርኅሩኆች ሁኑ"፤ እንደ ርኅሩኅ ማንነት ጌታን በየማለዳው መንካት ያስፈልገናል—ሰቆ. 3፡22-23፤ ሮሜ 9፡15 እና የግርጌ ማስታወሻ 2፤ ዘጸ. 34፡6፤ መዝ. 103፡8፤ ሉቃ. 1፡78-79፤ 10፡25-37፤ ሮሜ 12፡1።

**III. በአምስት እንጀራና በሁለት ዓሣ አምስት ሺህ ሕዝብ የመገበበትን ተዓምራት በማሳየቱ ጌታ ደቀ መዛሙርቱ ከእርሱ እንዲማሩ አሰለጠናቸው—ማቴ. 14፡14-21፤ 11፡28-30፦**

ሀ. ማቴዎስ 14፡19 አምስቱንም እንጀራና ሁለቱን ዓሣ ይዞ ወደ ሰማይ አሻቅቦ አየና ባረከ ይላል፦

1. *ወደ ሰማይ አሻቅቦ* ማየት የሚያመለክተው ወደ ምንጩ፣ በሰማይ ወዳለው አባቱ መመልከቱን ነው፦
   ሀ. ይህ የሚያመለክተው የበረከቱ ምንጭ እርሱ እንዳልሆነ መገንዘቡን ነው፤ የተላከው ሳይሆን አብ እንደ ላኪው የበረከት ምንጭ መሆን አለበት—ተዛ. ሮሜ. 11፡36።
   ለ. ማድረግ የምንችለው ምንም ያህል ቢሆን ወይም ምን ማድረግ እንዳለብን የምናውቀው ምንም ያህል ቢሆን በምናደርገው ነገር ላይ የላኪው በረከት እንደሚያስፈልገን መገንዘብ አለብን ይህም በራሳችን ሳይሆን በእርሱ በመታመን የአቅርቦት መተላለፊያዎች መሆን እንችል ዘንድ ነው—ተዛ. ማቴ. 14፡19፤ ዘኁ. 6፡22-27።
2. በሰማይ ወዳለው አብ መመልከቱ በሰማይ ባለው አብ እንደተላከ በምድር እንዳለ ልጅ፣ በአብ በመታመን ከአብ ጋር አንድ እንደነበር ያመለክታል—ዮሐ. 10፡10፦
   ሀ. የምናውቀው ነገር እና ማድረግ የምንችለው ነገር ምንም ማለት ናቸው፤ ከጌታ ጋር አንድ መሆንና በእርሱ መታመን ማለት በአገልግሎታችን ሁሉ ነገር ነው—ተዛ. 1 ቆሮ. 2፡3-4።
   ለ. በረከቱ የሚመጣው ከጌታ ጋር አንድ በመሆናችን እና በእርሱ በመታመናችን ብቻ ነው—ተዛ. 2 ቆሮ. 1፡8-9።
3. ጌታ ከራሱ ምንም ነገር አላደረገም—ዮሐ. 5፡19፤ ተዛ. ማቴ. 16፡24፦
   ሀ. ራሳችንን መካድ እና ምንም ነገር ከራሳችን የማድረግ ውጥን ያለን ሳይሆን ሁሉንም ነገር ከእርሱ የማድረግ ውጥን ያለን መሆን አለብን።
   ለ. እኔነትን ለመካድና በተትረፈረፈው የኢየሱስ ክርስቶስ መንፈስ አቅርቦት በሌላ ሕይወት ለመኖር ባለማቋረጥ መንፈሳችንን ማንቀሳቀስ ያስፈልገናል—ፊልጵ. 1፡19-21።
4. ጌታ የላከውን ፈቃድ እንጂ የራሱን ፈቃድ አልፈለገም—ዮሐ. 5፡30፤ 6፡38፤ ማቴ. 26፡39፣ 42፦
   ሀ. የራሱን ኃሳብ፣ ውጥኑንና አላማውን ውድቅ አደረገ።
   ለ. ሁላችንም ስለዚህ አንድ ነገር በንቃት መሆን አለብን—የሆነ ሥራን እንድንሠራ ስንላክ፣ ያንን እድል የራሳችንን ግብ ለመፈለግ መውሰድ የለብንም፤ መሄድ ያለብን የላከንን የጌታችንን ኃሳብ፣ አላማ፣ ግብ እና ውጥን በመፈለግ ብቻ ነው—ተዛ. 1 ጢሞ. 5፡2።
5. ጌታ የላከውን አብ ክብር እንጂ የራሱን ክብር አልፈለገም—ዮሐ. 7፡18፤ 5፡41፤ ተዛ. 12፡43፦
   ሀ. ስፍራ የሚፈልጉ መሆን የራስን ክብር መፈለግ ነው—ተዛ. 3 ዮሐ. 9።
   ለ. እኔነታችን፣ አላማችን እና ስፍራ መፈለጋችን በሥራችን ውስጥ ትልቅ አጥፊ "ትሎች" መሆናቸውን ማየት ያስፈልገናል፤ እነርሱን መጥላት መማር አለብን።

ለ. በምለሳው ሁልጊዜ በጌታ ጥቅም ላይ የምንውል ከሆነ፣ ለአንዱ አዲሱ ሰው ሲባል እኔነታችን መካድ አለበት፣ አላማችን ውድቅ መደረግ አለበት ስፍራ መፈለጋችንም መተው አለበት—ማቴ. 16፡24።

© 2020 Living Stream Ministry